- በአሁኑ ጊዜ የምንመሰክራቸው ሁሉም ግኝቶች እና ፍልሰፋዎች ከመገኘታቸው ወይም ከመፈልሰፋቸው በፊት ተጽፈዋል።
- አንድ ሰው ካሉት በጣም ውጤታማ መሣሪያዎች መካከል ጊዜ እና ትዕግሥት ወሳኞቹ ናቸው ።
- አንድ ሰው ስኬታማ ለመሆን መጣር የለበትም ፣ ይልቁንስ መጣር ያለበት ዋጋ ያለው ሰው ለመሆን ነው፤ ከዚያ ስኬት በራሱ ይመጣል።
- አንድ ሰው ስለ ከዋከብት ማለም አለበት፣ ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ ሁለት አግሮቹን መሬት ላይ ማድረግ የለበትም።
- የማይሳሳት የማይሠራ ብቻ ነው።
- የስኬት መዝገበ ቃላት "ይህ ቢሆን ኖሮ" እና "ግን" የሚሉ ቃሎችን አልያዘም።
- ስኬታማ ለመሆን በመጀመሪያ ስኬታማ እንደምንሆን ማመን አለብን።
- አንድ ሰው ምንም ያህል ከባድ ቢሆንበት እና በዙሪያው ያሉ ሰዎች ሊናደዱበት ቢችሉም ለሕይወቱ ወሳኝ የሚባሉ ውሳኔዎችን መወሰን አለበት።
- በማፈግፈግ እና በመሸሽ መካከል ትልቅ ልዩነት አለ።
- ሰዎች መቁረጥ የሚፈልጉት ፍሬያማ ዛፍን ነው።
- ዕውቀት ከሌለው ሰው ጋር መወያየት እና መጨቃጨቅ በሁሉም የቃል ትርጉም ኪሳራ ነው፤ ምክንያቱም ሰዎች ስህተታቸውን በቀላሉ አያምኑም።
- በጣም ጥሩ ከሆኑ ስሜቶች መካከል ምርጡ፣ መላው ዓለም ቢጠላህም ትክክለኛውን ውሳኔ በወሰንክ ጊዜ የሚሰማህ ስሜት ነው።

♦♦♦❍♦♦♦

ምን ያምር ትዕግሥት!

ይህ ታሪክ በመከራ ጊዜ ሁሉን ቻይ በሆነው አላህ ላይ ተስፋ አለመቁረጥን እና የትዕግሥትን ዳራ የሚያስተምር ግሩም ምሳሌ አስቀምጦ ያለፈ ታሪክ ነው። እናም "ትዕግሥት የማያንሸራትት ጉዞ ነው" እንደተባለውም ነቢዩላህ አዩብ የትዕግሥት

ምሳሌ ተደርገው የሚወሰዱ ነብይ ናቸው። እኚህ ነብይ ለከባድ አደጋ በተጋለጡበት ጊዜ በአላህ ትእዛዝ ላይ ያላቸውን ተዕግሥት፣ ጉጉት እና እርካታን በተመለከተ ትልቅ ትምህርት የሰጠ ነበር። ይህንንም መግለጽ በፈለገ ጊዜ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ አለ "ታጋሽ ሆኖ አገኘነው፡ ምን ያምር አገልጋይነት፡ እርሱ በጣም ተመላሽ ነው። [ሷድ፡44]"

የአላህ (ሱ.ወ) ነብይ አዩብ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን እና ከባለቤታቸው ጋር በሶርያ፡ ሻም በተባለች ከተማ ውስጥ በጸጋ እና በድሎት ይኖሩ ነበር። ነብዩላህ አዩብ የተፍሲር እና የታሪክ ምሁራን እንደሚሉት ብዙ ገንዘብ የነበራቸው፣ ለሰዎች መልካም፣ በአላህ ሕግጋት ላይ ጥንቁቅ፣ መሐሪ፣ ለድሆች አዛኝ፣ ወላጅ የሌላቸውን አሳዳጊ እና እንግዶቻቸውን አክባሪ፣ እንዲሁም በተሰጣቸው ጸጋ ሁሉ አላህን አመሥጋኝ እና በገንዘባቸው ላይ ያለውን የአላህ (ሱ.ወ) መብት በአግባቡ የሚፈጽሙ ታላቅ ነብይ ነበሩ። የነብዩ አዩብ ባለቤትም ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ስለሰጣት እና በባለቤቷ የተተረፈረፈ ጸጋ ደስተኛ እና አላህን አመሥጋኝ ነበረች።

የመከራው ጅምር አንድ ያለው ከባላቤታቸው በስተቀር ሁሉም ቤተሰቦቻቸው ሲሞቱባቸው እና የሰውነት አካላቸው በበርካታ ዓይነት በሽታዎች ሲጠቃ ነበር፣ አናም ጌታቸውን ከሚያወሱበት ልባቸው እና ምላሳቸው በቀር ምንም ጤናማ የሚባል አካል አልቀራቸውም ነበር። ነብዩላህ አዩብ በዚህ ሁሉ ሁኔታ ሳይከፋ ታጋሽ በመሆን፣ ሌሊትና ቀን፣ ጧት እና ማታ ፈጣሪያቸውን በማስታወስ ይገፉበታል። ከዚያ ህመሙ እየባሰባቸው ሰዎችም እየራቋቸው ሄዱ፣ ሁኔታዋ ከተዳከመው እና ከደኸየችው ሚስታቸው በቀር ለእርሳቸው የሚራራላቸው ጠፉ፣ ባለቤታቸው እሳቸውን ለመመገብ ስትል ሰው ቤት በደመወዝ እስከማገልገል ደርሳ ነበር። ይህንን የምታደርገው ትዕግስተኛ እና ባሏን ወዳጅ ሚስት ስለሆነች ነበር። መከራው በነብዩ አዩብ ላይ እየባሰ በሄደ ቁጥር፡ ትዕግስታቸው እና የአላህን (ሱ.ወ) ውሳኔ የሚቀበሉበት መንገድ እጅግ የሚገርም ነበር።

የነብዩ አዩብ ባለቤት ፍፁም ታማኝ ሚስት በመሆን ከባሏ ጋር ከአሥራ ስምንት ዓመቶች በላይ የኖረች ሲሆን ለባሏ በነበራት እንክብካቤ እና አዘኔታ እንደምሳሌነት የምትጠቀስ እንስት ነበረች።

ስለሆነም ነብዩ አዩብ በእርሳቸው ላይ የደረሰው ከባድ ህመም እና ከባባድ ፈተናዎች ቢኖሩም የተብቃቁ እና ታጋሽ ልብ ስለነበራቸው ለአንድ አፍታ እንኳን የመበሳጨት ስሜት አላሳዩም ነበር። ለዚህም ነው ሁሉን ቻይ የሆነው አላህ "ታጋሽ ሆኖ አገኘነው፡ ምን ያምር አገልጋይ፡ እርሱ በጣም ተመላሽ ነው።[ሷድ፡44]" ሲል የገለጻቸው። ይህ ማለት ደግሞ ተመላሽ እና በሕግጋተ-ውሳኔዎች ላይ ታዛዥነታቸውን የሚገልጽ ነው። ሱፍያን አስ-ሰውሪ ስለተሰቃዩ ሁለት ባሪያዎች ተጠየቀ፤ አንዳቸው ታጋሽ እና ሌላኛው በተሰጠው ነገር አመሥጋኝ ነበሩ። በማለት ሁለቱም ለእርሳቸው ተመሳሳይ እንደሆኑ ተናገረ። ምክንያቱም ሁሉን ቻይ የሆነው አላህ ሁለቱንም አገልጋዮቹን፡ አንዱን ታጋሽ ሌላኛውን በተሰጠው ነገር ላይ አመሥጋኝ ብሎ ስለገለጻቸው፤ ነብዩ አዩብን ሲገልጽ "ምን ያምር አገልጋይ" በማለት ነበር፤ ነብዩ ሱለይማንንም ሲገልጽ "ምን ያምር አገልጋይ" በማለት ነበር የገለጻቸው።

ከዚህ ሁሉ ስቃይ በኋላ ነብዩ አዩብ መከራው እንዲነሳላቸው ፈጣሪያቸውን አላህን (ሱ.ወ) ወደ መለመን ፊታቸውን አዞሩ። እንዲህም አሉ፡ "እኔ መከራ አገኘኝ፡ አንተም ከአዛኞች ሁሉ ይበልጥ አዛኝ ነህ። [አል-አንቢያእ፡ 83]" እንዲሁም "እኔ ሰይጣን በጉዳትና በስቃይ ነካኝ። [ሷድ፡ 41]" አሉ። ነገሮች እንዲሆኑ በፈለገ ጊዜ በማድረግ ችሎታው ገደብ የሌለው አላህ የነብዩ አዩብን ልመና በመስማት ምላሽ ሰጣቸው። የሚከተለውን እፎይታ አዘል መለኮታዊ ትእዛዝም አስተላለፈ፡ "በእግርህ (ምድርን) ምታ፡ ይህ ቀዝቃዛ መታጠቢያም መጠጥም ነው። [ሷድ፡42]" አላቸው።

በዚህም መሠረት አላህ (ሱ.ወ) መልዕክተኛው አዩብን ምድሪቱን በእግራቸው እንዲመቱ ያዛቸዋል። ንፁህ የተፈጥሮ ውኃም ትፈልቃለች፤ ከፈለቀችው ውኃም

እንዲጠጡ እንዲታጠቡም ያዛቸዋል። የዚህን ጊዜ ውኃውን ሲጠጡ ሆዳቸው ውስጥ ከነበረው ሁሉ በሽታ የተፈወሱ ሲሆን፣ ሲታጠቡ ደግሞ ሌላው የሰውነታቸው አካል በሙሉ ተፈወሰ።

ከረዜ በኋላ ነብዩ አዩብ በጤነኛነት እና በጥሩ ስሜት ላይ በመሆን ነበር በእግራቸው እየተራመዱ ወደ ባለቤታቸው የተመለሱት፤ ያቺ ትዕግሥተኛ ሚስት አሳቸውን ባየች ጊዜ ግን ልታውቃቸው አልቻለችም፣ ይልቁንስ በሽታው ባለቤቷን ከመግደሉ በፊት ከባለቤቷ ጋር የሚመሳሰል ሰው መስሎ ታያት፣ እርሷም የታመመውን ባለቤቷን መግገኛ ያውቅ እንደሆን ጠየቀችው፣ በመቀጠልም ባላቤቷ ጤነኛ በነበረበት ወቅት ሰውየውን ይመስል እንደነበር አወሳችለት፣ ይህ ታጋሽ የአላህ (ሱ.ወ) መልዕክተኛም እኔ አዩብ፣ የድሮው ባለቤትሽ ነኝ ይሏታል። ቀጥለውም ፈጣሪያቸው ከዛ ሁሉ በሽታ እንደፈወሳቸው እና ወደ ጸጋቸውም እንደመለሳቸው የሚያወሳውን የቁርዓን አንቀጽ አነበቡላት "ለእርሱም ከእኛ ዘንድ ለችሮታ ባለ አዕምሮዎችንም ለመገሰጽ ቤተሰቦቹን ከእርሱም ጋር መሰላቸውን ሰጠነው። [ሷድ:43]"

ምንም ማድረግ የማይሳነው አላህ ቤተሰባቸውን ወደ ቀድሞ ከፍታው መለሰው፣ የቤተሰባቸውን ቁጥርም እንደድሮው እንዲበዛ ዘራቸውም እንዲሰፋ አደረገላቸው፣ ከነበረው ቁጥርም በእጥፍ አሳደገላቸው። የውስጡንም የውጩንም የሰውነት አካል ጤንነታቸውን የመለሰላቸው አላህ፡ ወስዶባቸው የነበረውን ሀብታቸውን እና ልጆቻቸውን እጥፍ ድርብ አድርጎ መለሰላቸው። አንተ ተስፋ የቆረጥክ ወንድሜ እንደ ነብዩላህ አዩብ ዓይነት ጉዳት በአንተ ላይ ደርሶ ነበር? እስኪ አስተንትን!

- ሁሉንም ወንዶችና ሴቶች ልጆችህን አጥተሃል?
- ሁሉንም ገንዘብህን አጥተሃል?
- የውስጡንም የውጩንም የሰውነት አካልህን ጤንነት አጥተሃል?
- ሁሉም ሰዎች አግልለውህ ነበር? እርቀውህስ ነበር?

እንደ ነብዩ አዩብ ሽልማት በመፈለግ ለዓመቶች በመከራ ውስጥ በቆየህ ጊዜ ታጋሽ ነበርክን? በምህረቱ ተስፋ ስትቆርጥ እና የእርሱ ደስታ ሲርቅህ፣ ይቅር እንዲልህ ወደ ጌታህ ለመጸለይ እጆችህን ከፍ የምታደርግበት ጊዜ አሁን አይደለምን?

> **<u>መልዕክት 11:</u>** ዓይንህን ወደ ሰማይ በማንጋጠጥ ጌታ ሆይ ተስፋ ስጠኝ እና ጭንቀቴንም አስወግድልኝ፣ በዚህ ነገር ላይ ችሎታ ያለህ አንተ ብቻ ነህ እና እያልክ ለምነው። ነብዩ አዩብ ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁንና "እኔ መከራ አገኘኝ፡ አንተም ከአዛኞች ሁሉ ይበልጥ አዛኝ ነህ። [አል-አንቢያእ፡ 83]" እንዳሉት በል።

❖❖❖◯❖❖❖

ሰምን ተስፋቢስ ትሆናለህ?

ተስፋቢስነት ማለት አጽናፈ ሰማይን እና ምድርን እንዲሁም ይህችን ዓለም በጥላቻ መመልከት ማለት ነው። ተስፋቢስ የሆነ ሰው ሁሉንም ነገር ጨለማ አድርጎ ነው የሚስለው፣ አበባው ሳይሆን እሾኹ ነው የሚታየው፣ የዘቢብ ፍሬ ለርሱ መራራ ነው። ጅብ እንኳን ቢመለከት ቦምብ ያየ ይመስል ነው የሚደነብረው፣ ዝናቡም እሳት መስሎ ነው የሚታየው። ተስፋቢስ የሆነ ሰው የተሳሰረ ግንባር ፣ የማይፈታ ፊት እና የተጨነቀች ነፍስ ያለው ነው። ይህ ሰው ተስፋም፣ እፎይታም፣ ሐሴትም የሌለው ሲሆን ነገሮችን የማቅለል ችሎታ የለውም። ይህ ሰው ሌሊቱ እነደማይነጋ፣ ድህነቱ እንደሚቀጥል፣ ረሃብ ሁሌም እንደሚዘልቅ፣ ከታመመ እንደማይሽር ብቻ ነው ያሚያስበው። የዓረብኛው መዝገበ ቃላት ተስፋቢስ የሚለውን ቃል ሲተረጉም ሞት፣ በሽታ፣ ጥፋት ፣ ውድቀት ፣ ብስጭት እና መንሸራተት ሲል ያስቀምጣል። አላህም (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል "ጩኸትን ሁሉ በእነርሱ ላይ ነው ብለው ያስባሉ።[አል-ሙናፊቁን፡4]"

ተስፋቢስ የሆነ ሰው በየቀኑ አንድ ጊዜ ይሞታል፣ ሆዱ ሞልቶም የተራበ ነው፣ ሀብታም ሆኖም ድሃ ነው፣ ይህ ሁሉ ከአላህ (ሱ.ወ) ይልቅ ለሰይጣን ታዛዥ መሆኑን

ያሳያል። ሁሉን ቻዩ አላህ እንዲህ ይላል: "ሰይጣን (እንዳትለግሱ) ድኽነትን ያስፈራራችኋል። በመጥፎም ያዛችኋል። [አል-በቀራ:268]" ተስፋቢስ ሰው: "ባሮቼ ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው): እኔ ቅርብ ነኝ። [አል-በቀራ:186]" የሚለውን የአላህ ንግግር እንኳን አንብቦ አያስተነትንም።

- እሱ ላንተ ቅርብ ነው፤ ይሰማል ይመልሳል፣ አሩቅም ቅርብም ያሉትን ይሰጣል።
- እሱ ላንተ ቅርብ ነው፤ ድርቅ ለሆነባቸው ያዘንባል፣ የተራቡትን ያጠግባል፣ የተጠሙትን ያረካል፣ ምጽዋትንም ያስከትላል።
- እሱ ላንተ ቅርብ ነው፤ ሰጪ ነው፣ መልካምነቱ ይመጣል ይሄዳል፣ በሩ ሁሌም ክፍት ነው፣ ለጋስ እና ይቅር ባይም ነው።
- እሱ ላንተ ቅርብ ነው፤ አገልጋይ ባሪያውን በዋሻ ውስጥ ነፃ አናዳወጣው፤ በባህሩ ውስጥ የሰጠመውን፣ በበረሃ የጠፋውን እና ከግንቡ ጀርባ የታሰረውን ሁሉ ነፃ አውጥቷል።
- እሱ ላንተ ቅርብ ነው፤ ደስታው እና እፎይታው በዓይን ብልጭታ ውስጥ ነው፣ የተሸነፈ በለመነው ጊዜ ያሸንፋል፣ ይመለከታል አናም ሽፋን ይሆናል፣ ያውቃል ይቀርም ይለዋል፣ ያመለኩትንም ያመሰግናል፣ እና በችግር ጊዜ የታገሱትንም ይረዳል።
- እሱ ላንተ ቅርብ ነው፤ ፍፁም ጠንካራ ሲሆን ተስተካካይም ሆነ ተፎካካሪ የለውም፣ ለባሪያው ከሀብለ-ሠረሠሩ በበለጠ የሚቀርብ ነው፣ በሕይወት ካሉትም ከተሰውትም ሁሉ ተመሥጋኝም ተወዳሽም እሱ ነው።
- እሱ ላንተ ቅርብ ነው፤ ኃጢአተኞችን ለንሰሐ ተጣርቷል፣ ይቅርታን ለሚጠይቁት በሩን ከፍቷል፣ ያለ ምንም ሒሳብ ለባሪያዎቹ ይመጸውታል።

<u>መልዕክት 12:</u> በእውነት ራስህን ጠይቅ: በእውነትም መልስ ስጥ: ከዚህ ሁሉ የአላህ (ሱ.ወ) ጸጋ በኋላ ተስፋቢስ ትሆናለህ?

♦♦♦◯♦♦♦

ፔፕሲ ኮላ

የፔፕሲ ኮላን ጣዕም ያልቀመሰ ይኖር ይሆን? ይህ በሚሊዮኖች የሚጎነጨት እና በፕላኔቷ ዙሪያ በ195ቱም ሃገራት ከአጽናፍ አስከ አጽናፍ የተሰራጨው ለሥላሳ መጠጥ፡ የምግብ አለመፈጨትን ለማከም ይፍጨረጨር በነበረ አንድ የመድኃኒት ቀማሚ ጭንቅላት ውስጥ የተጠነሰሰ ቀላል ሀሳብ ነበር፤ እና በዚህ ዓለም ላይ የመብል እና የመጠጥ ዘይቤን የቀየረ ጣፋጭ እና ለሥላሳ መጠጥ ባገኘ ጊዜ፡ ከትልልቁ ሰው ይልቅ ልጆች እና ወጣቶች ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘ መጠጥ ሆነ።

ካሌብ ብራድ ሀም እንዴት ይህን ግኝት ሊያገኘው ቻለ?

በመድኃኒት ቤቱ ውስጥ የዕለት ተዕለት ተግባሩን በሚያካሂድበት ወቅት በማዘዣ ወረቀቶቹ መሠረት መድኃኒቶችን ማደባለቅ የጀመረ ሲሆን በሥራው ወቅት አንድ ረዳት ቀጥሮም ያሠራ ነበር፤ ይህም የፍራፍሬ ቃና ያለው ሽሮፕን ከሶዳ ውኃ ጋር በማቀላቀል በማስቻል ረዳው። የ22 ዓመቱ ብራድ ሀም በ1898 እ.ኤ.አ ሞቃታማ እና ወበቃማ በሆኑት የበጋ ቀኖች ውስጥ፡ ለፋርማሲ ደንበኞቹ ጣፋጭ እና ለሥላሳ መጠጥ በመቀመም ማቅረብ ጀመረ፤ ይህ መጠጥ በአጭር ጊዜ ተወዳጅነትን በማትረፍ ያልተጠበቀ ስኬትን አስገኘ።

ብራድ ሀም ይህን ልዩ መጠጥ "ፔፕሲ-ኮላ" ብሎ ለመሰየም ወሰነ፤ ምክንያቱም ዲስፔፕሲያ (Dyspepsia) በመባል የሚታወቀውን በሽታ በማከም ላይ ያገኘው ግኝት ስለነበር። ፔፕሲ ኮላ በጣም ተወዳጅ ሲሆን ብራድ ሃምም ይህንን ለሥላሳ እና ጣፋጭ መጠጥ ለማስተዋወቅ ተነሳሳ፤ ኩባንያ መክፈት አሳማኝ እና አስገዳጅ አስኪሆንበት ድረስ ሰዎች ለመግዛት እና በብዛት ለማዘዝ ተጣደፉ፤ ካሌብም መጠጡን ለገበያ ለማቅረብ ተገደደ።

እ.ኤ.አ በ1902 ከፋርማሲው የኋላ ክፍል የፔፕሲ ኮላ ኩባንያን አቋቁሞ የባለቤትነት መብቱን አንዷ ንግድ ሥራ ፈጠራነት ለማስመዝገብ የባለቤትነት ማረጋገጫ ጥያቄ አቅርቧል፤ በመጀመሪያ መጠጡን ቀላቅሎ በሶዳ ውኃ ማሽኖች

በኩል ነበር የሚሸጠው፣ ግን ፍላጎቱ "የፈጠራው ባለቤት መሆን ስለነበር፤ ብራድ ሃም ፔፕሲን በትንሽ ጠርሙሶች በማሸግ ለመሸጥ ወሰነ፣ በዚህም ምክንያት በየትኛውም ቦታ ሊጠጣ የቻለ መጠጥ ሆነ።

ንግዱ በከፍተኛ ሁኔታ ባደገ ቁጥር እ.ኤ.አ. ሰኔ 16 ቀን 1903 ፔፕሲ ኮላ የባለቤትነት የንግድ ምልክቱን በአሜሪካ ውስጥ ከሚገኘው የንግድ ምልክት እና የምርት ስም ምዝገባ መሥሪያ ቤት ያገኘ ሲሆን፤ በይፋ "መታደስ፣ መጠንከር እና የምግብ መፈጨት በፔፕሲ ኮላ" የሚል ማስታወቂያ በመሥራት፡ በዚያው ዓመት ካሌብ 7,968 የፔፕሲ ጠርሙሶችን መሸጥ ቻለ። በመቀጠልም በብረት ጣሳዎችና በጠርሙሶች ውስጥ ፔፕሲን በመሙላት ሀጋዊ ባለቤት ሆኖ መሸጥ የጀመረ ሲሆን፤ ኩባንያው ቁጥሩን በ1905 ከነበሩት ሁለት ቅርንጫፎች፣ በ1906 ወደ 15 ቅርንጫፎች፣ እንዲሁም በ1907 ደግሞ ወደ 40 ቅርንጫፎች አሳድጓል። በ1910 እ.ኤ.አ. በፔፕሲ ንብረትነት የፔፕሲ ኮላ ምርት በ24 ግዛቶች ውስጥ ቅርንጫፎች ያሉት ኩባንያ ሆነ። ይህ ስኬት ብራድ ሀም ካደረጋቸው እጅግ አስፈላጊ ነገሮች አንዱ ሲሆን የድርጅቱን ሽያጭ በዓመት ወደ 100,000 ጋሎን መጠጥ አሳድጎለታል።

ከ17 የስኬት ዓመቶች በኋላ የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት መጣ እና ፔፕሲ እንደገና ችግር ውስጥ ገባ፣ በዙሪያው በሚከናወነው ነገርም ተጎዳ፣ የስኳር ዋጋ በአደገኛ ሁኔታ ተለዋወጠ፣ ይህም የፔፕሲ ኮላ ምርት ላይ ትልቅ ተጽዕኖ አሳደረ፤ በዚህም ምክንያት ብራድ ሃም ኩባንያውን አደጋ ላይ ላለመጣል እና ኃላፊነት በመውሰድ ስምምነቶችን በማድረግ ኩባንያው ሳይወድቅ መቀጠል እንዲችል አድርጓል። ከ 3 አድካሚ ዓመቶች በኋላ ስኳርን በከፍተኛ መጠን ያከማቸ ቢሆንም፡ የዕድል ነገር ሆነና በኋላ ላይ የስኳር ዋጋ በተደጋጋሚ ጊዜ በመውረዱ ከስረት አጋጥሞትም ነበር፤ በመጨረሻም በ1924 እ.ኤ.አ. የቀሩት 2 የፔፕሲ ፋብሪካዎች ብቻ ነበሩ።

ብራድ ሀም ወደ ሱርማሲው ተመልሶ የፔፕሲውን ስም በሽያጭ አሰራጨው፣ በእርግጥም ለሮይ ሜጋን ጊል (Roy Megan Gill) ሽጦለት ነበር፣ ከዚያ በኋላ አራት የስም ባለቤቶች ስኬታማ ሆነዋል፣ ግን ቼኮላቴር (chocolatier) በመባል የሚታወቀው ቻርለስ ኬም ጉዝ (Charles came Guth) የተባለው ገሾ ሲቀር ሁሉም ፔፕሲን ወደ አቋሙ ማምጣት አልቻሉም ነበር። ቻርለስ ፔፕሲን ከውድቀት የታደገ ሰው ሆነ። ምክንያቱም ኩባንያው የእርሱን ሀሳቦች እና ልምዶቹን በማግኘቱ ነው። ከ15 የውድቀት ዓመቶች በኋላ እና በ58 ዓመቱ ያረፈው ብራድ ሀም ከከሰረበት ቀን ጀምሮ ማለትም ከአስር ዓመቶች በኋላ ኩባንያው አንደገና በሁለት እግሩ ሊቆም ቻለ።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ኩባንያው ወደኋላ ተመልሶ በድህነት እና በኢኮኖሚ ቀውስ ይሰቃይ ጀመር። እናም ሰዎች ለአንድ ለሥላሳ መጠጥ 5 ሳንቲም አንኳን መክፈል አስኪያቅታቸው ድረስ፤ የዚህን ጊዜ ነበር ሮዝ በተመሳሳይ ዋጋ የፔፕሲን መጠን በእጥፍ በማሳደግ ከሌሎች የመጠጥ ኩባንያዎች ጋር መወዳደር እንዲችል ያደረገው። እናም ፔፕሲ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ አንደገና በአዳዲስ ሀሳቦች፣ በአዳዲስ መፈክሮች እና ማስታወቂያዎች እንደገና መነሳሳት ጀመረ።

ዛሬ ፔፕሲ ኮላ በዓለም ላይ ካሉ ምርጥ ኩባንያዎች አንዱ እንደሆነ ይታመናል፡ በአሜሪካ ውስጥ ከሚገኙ 500 ኩባንያዎች መካከል በ21ኛ ደረጃም ተቀምጧል።

> <u>መልዕክት 13፡</u> አንድ ታላቅ ምኞት የታከለበት ቀላል ሀሳብ በዓለም ዙሪያ ሁሉ የተዳረሰን ጥቁር መጠጥ አስገኘ እናም ይህ መጠጥ ወንዞችን ሊሞላ በሚችል መጠን በሁሉም የዓለም ጠርዞች ተሰራጨ። ውድቀቶች እና ወጥመዶች ቢኖሩም ለስኬት ቁርጥ ያለ ውሳኔ ያስፈልጋል!

♦♦♦◯♦♦♦